Amharic | አማርኛ



# ስለ ልጄ እጨነቃለሁ

የሆነ ችግር ሊፈጠር ይችላል ብለው ለሚጨነቁ ወላጆች እና ተንከባካቢዎች መመሪያ። ይህ ቡክሌት የማስጠንቀቂያ ምልክቶችን እንዲያውቁ፣ ግሩሚንግ (ኣንድን ህጻን ለጾታዊ ግንኙነት የማዘጋጀትና የማነሳሳት ተግባር) እንዲረዱ፣ ይፋ ማድረጊያዎችን እንዲያዳምጡ እና እርዳታ ሲፈልጉ ምን ማድረግ እንዳለቦት ለማወቅ ይረዳዎታል።

የጋራ ተነሳሽነት

Body Safety Australia

GENWEST

የ GENWEST የጋራ ተነሳሽነት የቪክቶሪያ መንግስትን ድጋፍ እውቅና ሰጠ

VICTORIA State Government

# ስለ ደራሲዎቹ

**Body Safety Australia (የሰውነት ደህንነት አውስትራሊያ)** ልጆች ፍትሃዊ እና አክብሮት ያለው ግንኙነት የሚደሰቱበት ከጥቃት ነጻ የሆኑ የልጅነት ጊዜዎችን ያበረታታል።

ከመስመር ውጭም ሆነ በመስመር ላይ በልጆች ላይ በታዳጊ ወጣቶች ላይ የሚደርሰውን ጥቃት ለመከላከል በማስረጃ ላይ የተመሰረቱ ፕሮግራሞችን ለልጆች፣ ወጣቶች፣ ቤተሰቦች እና ማህበረሰቦች እናቀርባለን።

በበለጠ መረጃ ለማግኘት ድረገጽ **www.bodysafetyaustralia.com.au**

---

**GenWest** በሜልበርን ምዕራብ በቤተሰብ እና በሥርዓተ-ጾታ ላይ የተመሰረተ ጥቃትን ለመከላከል እና ምላሽ ለመስጠት ይሰራል። ሰዎች እና ማህበረሰቦች በማህበራዊ እና በጤና ትምህርት ፕሮግራሞች ደህንነቱ የተጠበቀ እና ጤናማ ህይወት እንዲኖሩ እንደግፋለን።

እንዲሁም የቤተሰብ ጥቃት የሚደርስባቸው ጎልማሶች እና ህጻናት ደህንነታቸውን እንዲጠብቁ እና የሚያስፈልጋቸውን እርዳታ እንዲያገኙ እንደግፋለን።

ለበለጠ መረጃ ድረገጽ **genwest.org.au**



**ምዕራፍ 1**

# ግሩሚንግ

ግሩሚንግ ማለት ልጆችን የሚበድል ሰው በልጁ እና በዙሪያቸው ካሉ ሰዎች ጋር መተማመንን ሲፈጥር በጊዜ ሂደት ያንን ልጅ ማግኘት ይችላሉ። መጀመሪያ ላይ ሁልጊዜ በግልጽ ጎጂ አይመስልም። በመተማመን ግንባታ እና ‘ልዩ’ ህክምና ሊከሰት ይችላል። ደህንነቱ ባልተጠበቀ መንገድ ድንበሮችን ቀስ በቀስ መጣስ ይችላል። ከአምስት ዓመት በታች የሆኑ ህጻናት በተለይ ለአደጋ የተጋለጡ ናቸው ምክንያቱም ምን እየተፈጠረ እንዳለ ለማብራራት ቃላት ላይኖራቸው ይችላል። ግሩሚንግ ብዙውን ጊዜ በደረጃ ይከሰታል። አዋቂዎች ካስተዋሉ እና ቀደም ብለው እርምጃ ከወሰዱ ግሩንግ በማንኛውም ደረጃ ሊቆም ይችላል።

# የግሩሚንግ ደረጃዎች



## መተማመንን እና መልካም ስም መገንባት

በደል የሚፈጽም ሰው ከቤተሰብ እና ከማህበረሰቡ ጋር መተማመንን ይፈጥራል። አጋዥ፣ ማራኪ እና አስተማማኝ በመባል ሊታወቁ ይችላሉ። ይህ እምነት ስጋቶችን በኋላ ላይ እንዲታወቁ ወይም እንዲጠየቁ አስቸጋሪ ያደርገዋል።




## ተጋላጭነቶችን ስለማግኘት

የበለጠ ተጋላጭነት ያላቸውን ቤተሰቦች ወይም ልጆች ሊፈልጉ እና ሊያነጣጥሩ ይችላሉ። ይህ በሌሎች እንክብካቤ ላይ የሚተማመኑ አካል ጉዳተኛ ልጆችን ወይም በተፈጥሯቸው የበለጠ ታዛዥ የሆኑትን ሊያካትት ይችላል። ይህ የቋንቋ መሰናክሎችን፣ የገንዘብ ችግርን፣ ማህበራዊ መገለልን ወይም አገልግሎቶችን ወይም ስልጣንን የመጠራጠር እድላቸው አነስተኛ የሆኑ ቤተሰቦችን ሊያካትት ይችላል።



## 'ልዩ' ትኩረት መስጠት

አዋቂው ለልጁ ከሌሎቹ የበለጠ ትኩረት ሊሰጥ ይችላል። ይህ ተጨማሪ ጊዜን፣ ስጦታዎችን፣ ምስጋናዎችን ወይም እንክብካቤን ሊያካትት ይችላል።



## ተገቢ ያልሆነ ባህሪ

ቀስ በቀስ አስተማማኝ ድንበሮችን ሊጥሱ ይችላሉ። ይህ ትንሽ ወይም ምንም ጉዳት የሌላቸው በሚመስሉ ባህሪያት ሊጀምር ይችላል፤ ለምሳሌ አላስፈላጊ መንካት ወይም በአካል በጣም መቅረብ። እነዚህ ባህሪያት ከጊዜ ወደ ጊዜ ቀስ በቀስ ሊጨምሩ እና የበለጠ ደህንነታቸው ያልተጠበቀ ሊሆኑ ይችላሉ.



## ኣለመናገር ዝም ማለት

ልጁ ለማንም እንዳይናገር ለማድረግ ሊሞክሩ ይችላሉ። ይህ ህጻኑ ሚስጥሩን እንዲይዝ መጠየቅ፣ ጉቦ መጠቀም፣ ማስፈራራት ወይም ህጻኑ ግራ እንዲጋባ፣ ኃላፊነት እንዲወስድ ወይም ለመግለጽ እንዲፈራ ማድረግን ሊያካትት ይችላል።

# በትናንሽ ልጆች (ከአምስት በታች) የማስጠንቀቂያ ምልክቶች



ከአምስት ዓመት በታች የሆኑ ህጻናት ምን እንደተደረገባቸው ማስረዳት ላይችሉ ይችላሉ። የባህሪ ለውጦች አስፈላጊ ምልክት ሊሆኑ ይችላሉ።

ወላጆች የሚከተሉትን መፈለግ ይችላሉ፡v

- **የአንድ የተወሰነ ሰው፣ ቦታ ወይም ተግባር ድንገተኛ ፍርሃት**
- **የእንቅልፍ ለውጦች (ቅዠቶች ወይም ከወትሮው የበለጠ ኣልጋውን ማራስ)**
- **የምግብ ፍላጎት ለውጦች (ከወትሮው በጣም ያነሰ ወይም የበለጠ መብላት)**
- **ከሚወዷቸው ሰዎች ጋር ባልተለመደ ሁኔታ መቀራረብ ወይም መራቅ**
- **በቋንቋ ወይም በባህሪ ወደ ኋላ መመለስ (ከወትሮው የባሰ እንደ ወጣት ሆኖ መሆን)**
- **ድንገተኛ የቁጣ ወይም የሀዘን ፍንዳታ**
- **የህፍረት ወይም የጥፋተኝነት ስሜት**
- **ከእድሜ ጋር የማይስማማ ስለ ወሲባዊ ባህሪ እውቀት**
- **ለእድሜያቸው በጣም ያደጉ የሚመስሉ ተግባር ሚናዎችን ወይም ባህሪያትን ማሳየት**





**የወላጅ ጽሁፋዊ ቅጂ (ስክሪፕት)፡**
*“በልጄ ባህሪ ላይ አንዳንድ ለውጦችን አስተውያለሁ እናም አሳስቦኛል። ምን እየሆነ እንዳለ እንድረዳ ልትረዳኝ ትችላለህን?”*

**የወላጅ ጽሁፋዊ ቅጂ (ስክሪፕት)፡**
*“ከልጄ እና ከሌላ ሰው ጋር በተያያዘ ስላየሁት አንድ ነገር እጨነቃለሁ። ምን አይነት ድጋፍ መስጠት እንደምትችል ማውራት እፈልጋለሁ።”*

**የወላጅ ጽሁፋዊ ቅጂ (ስክሪፕት):**
*“እንደተበሳጨህ አስተውያለሁ። ምቾት እንዳይሰማዎት ወይም እንዲፈሩ ያደረጋችሁ የሆነ ነገር ተከስቷልን?”*

**የወላጅ ጽሁፋዊ ቅጂ (ስክሪፕት)፡***“ምንም እንኳን ሚስጥር ቢሆንም እንድትፈራ ስለሚያደርግ ማንኛውም ነገር ልታናግረኝ ትችላለህ። አዳምጥዎት ኣለሁ፡ ችግር ውስጥ አይደለህም።”*





**ምዕራፍ 2**

# የመስማት ችሎታ መግለጫዎች

ከልጆች መግለጫዎችን ኣውጥቶ መስማት አስቸጋሪ ነው። ነገር ግን በእርጋታ ምላሽ መስጠት እና ተገቢውን እርምጃ መውሰድ አስፈላጊ ነው። ብዙ ልጆች ምን እንደተፈጠረ በትክክል ለማብራራት ቃላት አይኖራቸውም። የተከሰተው ነገር ትክክል እንዳልሆነ ላያውቁ ይችላሉ። ይህንን በባህሪያቸው፣ በጨዋታቸው፣ በስዕሎቻቸው፣ በተረት ተረት ወይም በትንሽ አስተያየቶቻቸው ሊገልጹት ይችላሉ። በእነዚህ ጊዜያት እንዴት ምላሽ እንደሚሰጡ ማወቅ አስፈላጊ ነው።

## ማድረግ

- ✓ ምላሽ ከመስጠትዎ በፊት ይረጋጉ እና በቀስታ ይተንፍሱ
- ✓ ልጅዎን ሳያቋርጡ ያዳምጡ
- ✓ ልጅዎን ይመኑ እና በቁም ነገር ይያዙዋቸው
- ✓ ልጅዎ ችግር ውስጥ እንዳልሆነ ወይም ጥፋተኛ እንዳልሆነ ማረጋገጥ።
- ✓ ለልጅዎ ስለነገሩዎት ደስተኛ እንደሆኑ ይንገሯቸው።
- ✓ ድጋፍ ለማግኘት ይድረሱ

## ኣለማድርግ

- ✗ በሚስጥር ለመያዝ ቃል አትግባ
- ✗ ብዙ ጥያቄዎችን አትጠይቁ ወይም ለመመርመር አይሞክሩ
- ✗ በልጁ ፊት በድንጋጤ፣ በቁጣ ወይም ባለማመን ምላሽ አትስጡ።
- ✗ ለተፈጠረው ነገር ልጅዎን አይወቅሱ ወይም አያሳፍሩት።
- ✗ ከባድ እንዳልሆነ ወይም ‘ትልቅ ጉዳይ አይደለም’ ብሎ ኣስተያየት ኣለመስጠት።
- ✗ ማድረግ ለማይችሉት ነገር ቃል ኣለመግባት (ዳግመኛ እንደማይከሰት ስለሚያደርግ)።



## አንድ ልጅ አንድ ነገር በቀጥታ ቢነግርዎት

**የወላጅ ጽሁፋዊ ቅጂ (ስክሪፕት):**
*“ለመናገር ዝግጁ የሆንከው ብቻ መናገር አለብህ። ስለነገርከኝ በጣም ጎበዝና ደፋር ነህ። እያዳመጥኩ ነው።”*

**የወላጅ ጽሁፋዊ ቅጂ (ስክሪፕት):***"ያ ሰው ያንን ለማድረግ ስለመረጠ አዝናለሁ። ጥሩ አይደለም። አምንሃለ።"*

## አንድ ልጅ ኣሳሳቢ የሆነ ባህሪ ካሳየ

**የወላጅ ጽሁፋዊ ቅጂ (ስክሪፕት):**
*“ስለ አንተ የሚያስጨንቀኝ ነገር አስተዋልኩ። አለሁ። ስለማንኛውም ነገር ልታናግረኝ ትችላለህ”*

## ልጁን ማረጋጋት

**የወላጅ ጽሁፋዊ ቅጂ (ስክሪፕት):** *“ይህን ስለነገርከኝ አመሰግንሃለሁ። በዚህ በጣም ደስ ብሎኛል። እኔን በመንገርህ ትክክለኛውን ነገር አድርገሃል።”*

## ቀጥሎ ምን እንደሚሆን ማብራራት

**የወላጅ ጽሁፋዊ ቅጂ (ስክሪፕት):**
*"በእንደዚህ ዓይነት ጊዜያት መርዳት የሚችሉ ሰዎች አሉ፣ እናም እኛን እንዲረዱን አነጋግራቸዋለሁ።*



## ልጅዎ ምን እንደተፈጠረ በግልጽ ለማስረዳት ካልቻለ

እድሚያቸው ከአምስት ዓመት በታች የሆኑ ትናንሽ ህጻናት ክስተቶችን በቃላት መግለጽ ኣይችሉ ይሆናል። ይህ በተለይ መናገር ላልጀመሩ፣ ለማይናገሩ ወይም አማራጭ ግንኙነትን ለሚጠቀሙ በጣም አስፈላጊ ነው። ትናንሽ መረጃዎች ብቻ ወይም በባህሪ ላይ ለውጦችን ሊያገኙ ይችላሉ። እያንዳንዳቸው እነዚህ ቁርጥራጮች በራሳቸው ምንም ትርጉም ላይኖራቸው ይችላል፤ ነገር ግን እየጨመሩ ከሄዱ እርዳታ መጠየቅ አስፈላጊ ነው፡

# ይህ ከተከሰተ፡

ያስተዋሉትን እመኑ

ያዩትን ወይም የሰሙትን በተቻለ ፍጥነት ይጻፉት

ቅጦችን ወይም የባህሪ ለውጦችን ይፈልጉ

ልጁ እንዲያብራራ ኣለማጨናነቅ

አስፈላጊ ከሆነ የባለሙያ ምክር ይጠይቁ ወይም ስጋቶችን ሪፖርት ያድርጉ።

የልጅዎን ደህንነት እና ድጋፍ በመጠበቅ ላይ ያተኩሩ።

## የባለሙያ እርዳታ ከመጠየቅዎ በፊት ሁሉንም መረጃዎች ማግኘት የግድ አያስፈልግዎትም።

## ስጋቶችዎን ሪፖርት ማድረግ ማለት ባለሙያዎች ቀጥሎ ምን ማድረግ እንዳለቦት ሊመሩዎት ይችላሉ።





ምዕራፍ 3

# ሪፖርት ማድረግ እና እርዳታ ፍለጋ መንገዶች

ሪፖርት ማድረግን መፍራት መረዳት ይቻላል። ብዙ ወላጆች በልጃቸው፣ በቤተሰባቸው ወይም በማህበረሰባቸው ላይ ምን ሊደርስ እንደሚችል ይጨነቃሉ። በዚህ መንገድ ሲሰማዎት ብቻዎን አይደሉም፣ እና በእያንዳንዱ እርምጃ እርስዎን ለመርዳት ድጋፍ አለ።



# የግዴታ ሪፖርት ማድረግ ምን ማለት እንደሆነ

በአውስትራሊያ ውስጥ አንዳንድ ባለሙያዎች ስለ ልጁ ደህንነት ከባድ ስጋቶችን ሪፖርት ማድረግ ይጠበቅባቸዋል። ይህ 'የግዴታ ማሳወቅ' ይባላል። ይህ ህገ ደንብ የልጆችን ደህንነት ለመጠበቅ እንጂ ቤተሰቦችን መቅጣት አይደለም። የልጁን ደህንነት እና ደህና መሆን ማረጋገጥ እንዲችሉ የግዴታ ሪፖርቶች ወደ ልጆች ጥበቃ አገልግሎቶች ይሄዳሉ። ቤተሰቦችም ድጋፍ ሊቀርብላቸው ይችላል።

# የተለመዱ ጥያቄዎች እና መልሶች

### ሪፖርት ለማድረግ ስም-አልባ ነውን?

አንዳንድ አገልግሎቶች ስምዎን ሳይገልጹ መረጃን እንዲያጋሩ ያስችሉዎታል። ሆኖም፤ ይህ ማንን እንደሚያነጋግሩ ይወሰናል። ዝርዝር መረጃዎችን ከማጋራትዎ በፊት መጠየቅ ይችላሉ።

### ቤተሰቦቼ ላይ ምን ይፈጠራል?

አብዛኛዎቹ ሪፖርቶች ወደ ድጋፍ ይመራሉ። አገልግሎቶቹ ምን እየተፈጠረ እንዳለ እና ምን ድጋፍ እንደሚያስፈልግ በመረዳት ላይ ያተኩራሉ።

### ልጄ ከእኔ ይወሰዳልን?

በአብዛኛዎቹ ሁኔታዎች ልጆች ከቤተሰቦቻቸው ጋር ይቆያሉ። ከወላጅ መወገድ የሚከሰተው በልጁ ደህንነት ላይ ከባድ እና ፈጣን አደጋ ካለ ብቻ ነው።

### ተሳስቼ ኖሮ ቢሆንስ ምን ይደረጋል?

እርዳታ በመጠየቅ ወይም ያለዎን ስጋት በማካፈል ችግር ውስጥ አይገቡም። እርግጠኛ ካልሆኑ ምክር መጠየቅ ሁል ጊዜ ምንም ችግር የለውም።

አንድ ሰው የልጆችን ደህንነት እንዴት መጠበቅ እንደሚቻል ከልጅዎ የልጅ እንክብካቤ፣ ትምህርት ቤት፣ የስፖርት ቡድን ወይም ማህበረሰብ ጋር እንዲነጋገር ለማድረግ **Body Safety Australia (የሰውነት ደህንነት አውስትራሊያን)** ያነጋግሩ።

# SASH, Support After Sexual Harm ፣ (ከጾታዊ ጉዳት በኋላ ድጋፍ)

ይህ አገልግሎት እድሜው ከ 0 እስከ 17 ዓመት ለሆኑ ህጻናት እና የጾታ ጉዳት ጥቃት ለደረሰባቸው እና ቤተሰቦቻቸው ነው።
ይህ የ Royal Children's Hospital አካል ነው።

**ስልክ:** 9345 6391
**ድረገጽ:** www.rch.org.au/sash
**የሚገኙበት ኣካባቢ:** RCH Parkville, Werribee, እና Melton. በድንገተኛ ቀውስ የ24 ሰዓት ድጋፍ አለ።

ማሳሰቢያ፡ ልጅዎ ከተጎዱት የቅድመ ልጅነት ጊዜ ትምህርት እና እንክብካቤ ማዕከላት በአንዱ ውስጥ ከሆነ፣ ወደ SASH መደወል ይችላሉ። ድጋፍ ለማግኘት ይፈቀድልዎታል እና እንዲጠቀሙ እንመክራለን።

SASH በሚከተሉት ሊረዳ ይችላል፡




- የልጅዎን የደህንነት ፍላጎቶች መረዳት።
- እንደ ወላጅ ወይም ተንከባካቢ ለእርስዎ ምክር እና ድጋፍ።
- ስለተፈጠረው ነገር ከልጅዎ ጋር ለመነጋገር።
- የድጋፍ እቅድ ማውጣት።

# የአካባቢ ድጋፍ አገልግሎቶች

**WestCASA**
ይህ ነጻ፣ ሚስጥራዊ አገልግሎት የወሲብ ጉዳት ላጋጠማቸው እድሜያቸው 12 ዓመት እና ከዚያ በላይ ለሆኑ ህጻናት እንዲሁም ተንከባካቢዎቻቸው እና ቤተሰቦቻቸው የሚቀርብ ኣገልግሎት ነው።

**ስልክ:** 9216 044
**ድረገጽ:** westcasa.org.au
**የሚገኙበት ኣካባቢ:** ወረቢ/Werribee፣ ከድጋፍ ጋር በቴሌ ሄልዝ በኩልም ይገኛል።

WestCASA በሚከተሉት ሊረዳ ይችላል፡

- የቡድን ስራን ጨምሮ ምክር እና ድጋፍ።
- ዶክተሮችን ጨምሮ ወደ ሌሎች አጋዥ አገልግሎቶች ሪፈራል መላክ።
- ይህንን ከፈለጉ እንደ ወሲባዊ ወንጀልን ሪፖርት የማድረግ ሂደት አጠቃላይ እይታን የመሳሰሉ ግምት ውስጥ ማስገባት። ለፖሊስ ሪፖርት ማድረግ ኣያስፈልግም።
- ለደህንነትዎ እቅድ ማውጣት።

***ሁሉም ድጋፎች በአሰቃቂ ሁኔታ የተደገፉ ናቸው። የችግር ተሞክሮው በቅርብም ሆነ ያለፈው ለደረሰ አገዛን ማግኘት ይችላሉ።***

**የህጻን ጥበቃ**

የቪክቶሪያ መንግስት የህጻናት ጥበቃ አገልግሎቶች ስለ ልጁ ደህንነት ስጋቶችን ይመረምራሉ። ስለ ህጻን የሚጨነቁ ከሆነ ሊደውሉላቸው ይችላሉ።

**ከስራ ሰዓት በኋላ**: 13 12 78 (ከሰዓት በኃላ 5pm እስከ ጥዋቱ 9am በሳምንት፤ ቅዳሜና እሁድ እና ህዝባዊ በዓላት ለ24 ሰዓታት)

**በስራ ሰዓታት**: ለኣካባቢዎ ህጻን መከላከያ ቦሮ ያነጋግሩ። ለኣካባቢዎ ያለን ቢሮ ለማግኘት በድረገጽ services.dffh.vic.gov.au/child-protection ላይ ገብቶ ማየት ወትም በስልክ 1300 360 391 መደወል።

**የቪክቶሪያ ፖሊስ: Sexual Offences and Child Abuse Investigation Team (SOCIT) (የጾታ ጥቃቶች እና የልጆች ጥቃት ምርመራ ቡድን)**

SOCIT ወሲባዊ ወንጀሎችን እና የህጻናት ጥቃትን የሚመረምር ልዩ የቪክቶሪያ ፖሊስ ቡድን ነው። በሂደቱ ውስጥ ልጆችን እና ቤተሰቦችን ለመደገፍ የሰለጠኑ ናቸው።

**ስልክ**: 000 ለድንገተኛ ችግር ወይም የኣካባቢዎ ፖሊስ ጣቢያ ወደ SOCIT ይልክዎታል።

**ማሳሰቢያ**: ከ SOCIT ጋር ለመነጋገር መደበኛ ሪፖርት ማድረግ አያስፈልግዎትም። መጀመሪያ ጥያቄዎችን መጠየቅ ይችላሉ




ምዕራፍ 4

# የሕክምና (ቴራፒዩቲካል) ምላሾች

ቴራፒዩቲካል ድጋፍ ጎጂ የሆነ ነገር ከተከሰተ በኋላ ልጆች እና ቤተሰቦች እርዳታ የሚያገኙበት አስተማማኝ ቦታ ነው። ለትንንሽ ልጆች፤ ይህ ብዙውን ጊዜ ከመናገር ይልቅ እንደ ጨዋታ፤ ስዕል እና ቀላል የእንቅስቃሴ ተግባሮች ሆኖ ይታያል። የመጀመሪያው ቀጠሮ ብዙውን ጊዜ ልጁን እና ቤተሰቡን ማወቅ እና ምን ድጋፍ እንደሚያስፈልግ መረዳት ነው። አስፈሪ አይደለም፤ እናም ቤተሰቦች ብዙውን ጊዜ በሂደቱ ውስጥ ከልጃቸው ጋር ሊቆዩ ይችላሉ። የህክምና ባለሙያተኞች/ቴራፒስቶች የአካል ጉዳተኛ ልጆችን ወይም የተለያዩ የግንኙነት ፍላጎቶችን ጨምሮ ለእያንዳንዱ ልጅ ድጋፍን ማስተካከል አለባቸው።

# ቀጠሮ በመጠባበቅ ላይ እያሉ ቤት ውስጥ ምን ማድረግ ይችላሉ

- **የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴዎችን በተቻለ መጠን ወደ መደበኛው ማቅረብ**
- **ልጅዎ ደህንነታቸው የተጠበቀ መሆኑን እና እነሱን ለመርዳት ኣብሯቸው እንዳሉ ብዙ ጊዜ ያረጋግጡ**
- **ቀላል፣ የሚያረጋጋ ቃላትን መጠቀም፡ *“አንተ ከእኔ ጋር በመሆንህ ደህንነትህ የተጠበቀ ነው”***
- **በእነዚያ ጊዜያት ሊናደዱ ወይም ሊገለሉ እንደሚችሉ እና በፍቅር ድጋፍ እንደሚያስፈልጋቸው መገንዘብ**
- **ለልጅዎ ምን እየተፈጠረ እንዳለ እና በማንኛውም ቀጠሮ ላይ ምን እንደሚጠብቁ ማሳወቅ**
- **የልጅዎን ፍላጎት ማዳመጥ**

**የወላጅ ጽሁፋዊ ቅጂ (ስክሪፕት)፡**
***“እንድንዘጋጅ በመጀመሪያው የግንኙነት ክፍለ ጊዜ ምን እንደሚሆን ልትነግሩኝ ትችላላችሁን?”***



## የአካባቢ ቴራፒዩቲክ አገልግሎቶች

በቀደመው ምዕራፍ (SASH, WestCASA) ውስጥ ያሉት አገልግሎቶችም የህክምና ድጋፍ ይሰጣሉ። ከዚህ በታች ያለው አገልግሎት በተለይ የቤተሰብ ጥቃት ለደረሰባቸው ህጻናት ነው።

## GenWest

GenWest የቤተሰብ ጥቃት ለተመለከቱ ወይም ላጋጠማቸው ህጻናት እና ወጣቶች የምክር እና የህክምና ቡድኖችን ይሰጣል። vአገልግሎት በሜልበርን ምዕራብ ኣካባቢ ለሚኖሩ እድሜያቸው ከ0 እስከ 18 ዓመት ለሆኑ ሰዎች ያቀርባል።

**ስልክ**: 1800 436 937

**ድረገጽ**: genwest.org.au





GenWest እና Body Safety Australia የምንሰራበት እና አገልግሎታችንን የምንሰጥበት ቦታ መሬት ሁል ጊዜ የአቦርጂናል መሬት እንደነበረ እና እንደሚሆን ይገነዘባሉ። ያለፉትን እና የአሁኑን ሽማግሌዎች አክብሮት እንሰጣለን።

በናርም/Naarm፣ በሜልበርን ምዕራብ፣ በኩሊን ብሔር የዉሩንድጄሪ/ Wurundjeri እና የቡኑሮንግ/Bunurong ህዝብ ላሉት የመጀመሪያ መንግስታት ማህበረሰቦች በኩራት እናደንቃለን። የበለጸገ ልዩነታቸውን፣ ባህላቸውን፣ ታሪካቸውን እና እውቀታቸውን እና ለዚህ ክልል ህይወት ላበረከቱት ከፍተኛ አስተዋፅዖ እናደንቃለን።

የቅኝ ግዛት ቀጣይነት ያለው ተጽእኖ፣ እንዲሁም የአንደኛ መንግስታት ህዝቦች ጥንካሬ እና ጽናት እንገነዘባለን እና ለመሬት መብት፣ ራስን በራስ የመወሰን እድል፣ ሉዓላዊነት እና ያለፉትን ኢፍትሃዊነት እውቅና ለመስጠት እየተካሄደ ካለው ትግል ጋር አጋርነታችንን እንገልጻለን።